# የአማራ ብሄረተኝነትን አደጋነቱ ለኢትዮጵያ አንድነት ወይስ ለጀዋር መሃመድ ለራሱ ? ጀዋር መሃመድ የዘለላት እዉነት

ሸንቁጥ አየለ

ጀዋር ማሃመድ ከአማራ በላይ አማራ ሆኖ ስለ አማራ ብሄረተኝነት በሞራል የታጀበ ትንታኔ ሰጠ::ከታች ያለችዉን የቪዲዮ ሊንክ ይመልከቷት::ጀዋር የአማራ ብሄርተኝነት ከኢትዮጵያኒስቶችም ከወያኔም የገጠመዉ ፈተና ያስለቅሳል ሲል ትንታኔ አቅርቧል::ጀዋር የአማራ ብሄረተንነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለኝ:: መነሻና መድረሻዉንም ሁሉ አዉቀዋለሁ ብሎ የአማራ ብሄረተኝተ ቁሱ ግን እኔ ነኝ ሳይለን አለፈ::

የአማራ ብሄረተኝነት ለምን እንዳማለለዉ ብልጡ ጀዋር ሳይደብቅ ነግሮናል:: ጎታቹን እና ኋላ ቀሩን የአንድነት አመለካከት የሚንድ ሀይል ሆኖ የወጣዉ የአማራ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ነዉ ሲል ጀዋር እንደ መጨፈር እየቃጣዉ ተንትኗል::ጀዋር እዚህች ጋ ነዉ ታላቅ ተስፋ እና ራዕይ የቋጠሮዉ::ተራማጅ የአማራ ብሄረተኝነት በጀዋር ገለጻ መሰረት የሚፈልገዉ የአማራን ሀገር ነዉ:: እናም የኦሮሞዉንም ሀገር ይቀበላል::በዚህም በሂደት የጀዋር ተስፋ እና ግብ እዉነት ትሆናለች::የአንድነት ሀይሉ ስለማይኖር ጀዋር ይዞት ሊሄድ የተነሳዉን የኦሮሞ ሀገር ሀይ ባይ ሳይኖር አንጠልጥሎ ይሄዳል ማለት ነዉ::የአማራ ተራማጅ ብሄረተኞችም እንደ ጀዋር ህልም የአማራ ክልል ብሎ ወያኔ የሰጣቸዉን ምድር ይዘዉ ይቀራሉ ማለት ነዉ::ይሄ እንግዲህ የጀዋር ተስፋ ነዉ::

ጀዋር ብልጡ ከአማራ ብሄረተኝነት ተስፋ ያደረጋት ነገር ይህች ነች::ጀዋር ከአማራ ብሄረተኝነት መጠናከር ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የሚያስችል ጉልበት እንደሚወለድ አስልቶ ዛሬ የአማራ ተቆርቋሪ ሆኖ ስለ አማራ ህዝብ መበደል መዝሙር እያሰማ ነዉ:: ያዉም ጣፋጭ መዝሙር:: ደግሞ ሲናገርስ ሲችልበት::በጣም ተቆርቋሪ ሆኖ ነዉ::

እዉነታዉስ ምን ይሆናል? እዉነታዉ እንደሱ አይደለም የሚሆነዉ::የአማራ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት: የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ወይም የትግሬ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት የሚባል ተረት ተረት የለም::ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት የሚባለዉ የቃላት ጨዋታን ለማሳለጫ እና ለአፍ ማጣፈጫ ነዉ:: ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነትን ወያኔም ሀያ አምስት አመት ሰብካታለች::

በምሳሌ ላስረዳ::የትገሬ ወጣቶች ከበሮአቸዉን አንግተዉ : ጠምንጃቸዉን አንግበዉ : በአረብ ብር እና በምዕራባዉያን ድጋፍ እየታገዙ ኢትዮጵያን እናፈርሳለን: ዲሞክራሲያዊ የትግሬ ብሄረተኝነትን ገንብተን ትግራይን ነጻ እናወጣለን እያሉ 17 አመታት ተዋጉ: ዘፈኑ: አስዘፈኑ: ቀሰቀሱ አስቀሰቀሱ::

እናም ተሳካላቸዉ እና ደርግ መዉደቅ ብቻ ሳይሆን በርግጠኝነት ከስሩ መገርሰስ ሲጀምር አንድ ቀን ሌሊት ቁጭ ብለዉ መከሩ::"ተከዜን እንሻገር ወይስ ከተከዜ ወዲህ እንቁም?" የሚል እዚህ ግባ የማይባል ግን ወሳኝ የሚመስል ጥያቄ ተነሳ:: ለይስሙላ "የተዋጋንዉ ትግራይን ነጻ ለማዉጣት ነዉ እንጅ ሌላዉን ኢትዮፕያን ነጻ ለማዉጣት አይደለም" የሚል አንድ ሁለት እንቶ ፈንቶ ሀሳብ ቀረበ::በዚህ ሀሳብም ሁሉም ፈገግ አሉ::ሁሉም በህብረት "ኢትዮጵያ እኮ ሀገራችን ናት" ብለዉ በአንድ ድምጽ እና በአንድ የከበሮ ድለቃ ስንኝ በልባቸዉም በአፋቸዉም ተስማሙ::

ወዲያዉም ወያኔዎቹ መላዉ ኢትዮጵያን ጠቅልለዉ ወደ ኪሳቸዉ ለመከተት ተፋጠኑ::ሆኖም ኢትዮጵያን ወደ ኪሳቸዉ ሲከቷት የገጠማቸዉ ፈተና ኢትዮጵያን በትግራይ ልክ ሰፍተዋታል እና ሁሉንም ነገር ትግሬ እና የትግሬ ህልም አድርገዉት ቁጭ አሉ::አስተሳሰባቸዉ ስግብግብ : ሽፋፋ : መርዘኛ ተንኮለኛ እና አጥፊ ነበር እና የዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት መዝሙራቸዉን ከከበሮ ድለቃቸዉ ጋር ለሁሉም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች እያነሱ በወሬ ደረጃ ይለጥፉት ያዙ::ግን ሁሉም ነገር የትግሬ ህልም እና የትግሬ ጉዳይ ብቻ ሆኖ ቁጭ እንዲል መልሶ ህወሃት ይባትት ያዘ::

ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት አሸናፊ ሲሆን የመጨረሻዉ ግቡ ይሄዉ ነዉ::ኦሮሞም ቢያሸንፍ: አማራም ቢያሸንፍ: ትግሬም ቢያሸንፍ: ጉራጌም ቢያሸንፍ የዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት መገለጫዉ አንድ ነዉ::ስግብግብነት እና ራስ ወዳድነት በመጨረሻም የሌሎችን ህልዉና ማጥፋት ነዉ:: ህዉሃት የቀፈቀፋቸዉ የትግራይ ጭቃ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኞች አምስት ሚሊዮን አማራን ከምድረ ገጽ አጥፍተዉ አሁን ድረስ ሳያፍሩ እና ሳይደናገጡ አይናቸዉን አፍጥጠዉ ስለ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት የሚለፋት እና ስለ ብሄሮች እኩልነት የሚዘላብዱት የዲሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት መገለጫ ባህሪዉ ይሄዉ ሀሰት እና ሸፍጥ ስለሆነ ነዉ::ጀዋር ማህመድ በወያኔ አስተምህሮት የተቀረጸ : ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ጥላቻን በወያኔ የተጋተ : ይሄኑን ጥላቻዉን ከነብስ አባቱ ኦነግ የወረሰ: ግን ደግሞ የአክራሪ እስልምናን ህልም በልቡ ያነገበ ብልጥ የጥፋት ሀይል ነዉና ሁሉንም የተንኮል እና የጥፋት ስልቶች ሁሉ አቀናብሮ በመጠቀም ኢትዮጵያ የሚለዉን ሀገር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነቃቅሎ ለመጣል የሚተጋ ጉልበታም የኢትዮጵያዊነት አጥፊ ሀይል በመሆን ተከስቷል::

እናም ጀዋር ብልጡ እንደሚመኘዉ የአማራ ብሄረተኝነት ጠንክሮ ከወጣ እና አሸናፊ ከሆነ ወያኔ የከለላትን የግንባር ስጋ የምታክል የአማራ ክልል የምትባል መሬት ታቅፎ ይቀራል ብሎ ማሰብ እጅግ የሞኝ ፖለቲካ ነዉ::የኢትዮጵያ ሰዉ ሳንደባበቅ ስነልቦናዉ አንድ ነዉ::ሚዛናዊ ሁኔታዎች በሚጠፉበት ጊዜ ሁሉም ወገን በልቡ ተስፋፊ እና ወራሪ ነዉ::ጀዋር ነብሴ የኢትዮጵያን ህዝብ ቁጭ በሉ በሚል ስልት ልታታልለዉ የኛ ብሄረተኝነት ዲሞክራሲያዊ ነዉ ብትልም ቅሉ እድሉ ከቀናህ መላዉ ደቡብ ኢትዮጵያን ብሎም አማራን እንዲሁም ቀሪዉን ኢትዮጵያ ሁሉ በተስፋፊነት እንደምትዉጠዉ እሙን ነዉ:: ያዉም እስላማዊ መንግስትህን በልብህ አንግበህ የምትራመድ ተስፋፊ እንደምትሆን ሳይታለም የተፈታ ነዉ:: ዋናዉ ግብህም የሚሆነዉ ኢትዮጵያ የሚለዉን ሀገር ነቃቅለህ መጣል ይሆናል::

ጀዋር ብልጡ: ጀዋር ሞኙ ! ምክር አይገባህም እና አንተን መምከርም ድካም ነዉ::ግን እዉነታዉን እንድትረዳዉ አንድ ሀቅ እዚህ ማስፈር ይገባል::ይሄም ምንድነዉ::የኦሮሞም ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነትም ሆነ የአማራ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት አንተ እንደምትለዉ ተግባብቶ ጎን ለጎን

አይኖርም፡፡እርስ በርሱ ይጠፋፋል፡፡አንተም ይሄን ታዉቃለህ፡፡ለጊዜዉ ኢትዮጵያ አንድነት የሚለዉን አስተሳሰብ የያዘዉ የአማራዉ ምሁር ስለሆነ የኢትዮጵያ አንድነትን ከህዝቡ ህሊና ለመፋቅ የአማራ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነትን እናበረታታ የምትል የቁጭ ይበሉ ስሌት ይዘህ እየሰራህ መሆኑን እኛም ገብቶናል፡፡ እናማ የማንኛዉም አይነት ዲሞክራሲያዊ የሚባል የጎሳ ብሄረተኛነት ፍጻሜዉ እርስ በርስ መጠፋፋት፡ መዋዋጥ ብሎም እንደ ማሳለጫ ደግሞ የማያባራ የብሄሮች የርስበርስ ፍክክር እና ንትርክ ዉስጥ መዉደቅ መሆኑ ላንተ ይጠፋሃል ብዬ አላስብም፡፡ በዚህም አገር የሚለዉ ነገር ግብዓት ፍጻሜዉ በአስተማማኝ እንደሚከስም እሙን ነዉ፡፡ ያንተም ዋና ግብህ ይሄዉ ነዉ፡፡
አንተ ሲመችህ ክርስቲያን ኢትዮጵያንን በሜንጫ ስለመከትከት እየሰበክህ፡ አንዴ በዝግ ቤት ዉስጥ የኦሮሞን ህዝብ ከኢትዮጵያ መለያያ ቻርተር እያረቀቅህ ሌላ ጊዜ ያንተ ብጤዎችን ሰብስበህ ኢትዮጵያ ትፍረስ ትበታተን እያለህ፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ አክራሪ የእስልምና ህሳቤህን በሙስሊም ኢትዮጵያዉያን መሃከል በመዘራት በኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ ትግል የእስልምና ትግል ነዉ ብለህ ወደ ሀይማኖት ቁልቁለት እየተንሸራተትህ አሁን ደግሞ ተንደርድረህ ሳታፍር አይንህን በጨዉ ታጥበህ ስለ አማራ ህዝብ መበደል ብሎም ስለ ዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ፍቱን መፍተሄነት ሰበካ ይዘሃል፡፡

እናም መፍትሄዉ ምን ነበር? መፍተሄዉስ ቀላል ነበር፡፡ግን ከኢትዮጵያ አንድነት አራማጅ ሀይሉም ዉስጥ እንዳንተዉ አይነት ልባቸዉ የጠቋቆረ መሰሪዎች አሉ እና ነገሮች ሁሉም ይወለጋገዳሉ፡፡ እንዲሁም ከብሄር ፖለቲካ አራማጅ ሀይሎችም ዉስጥም እንዳንተዉ ነገሮችን በዛሬ ጠባብ መነጽር የሚመለከቱ ሀይሎች በዙ እና በረከቱ እንጅ መፍተሄዉስ አንተ ያጣጣልከዉ እዉነታ ነበር፡;አንተ በማያፍር እና በባለጌ አንደበትህ የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይን እንደ ተንኮለኛዉ መለስ ዜናዊ የድሮ ስርዓት ናፋቂዎች ህልም ነዉ ብለህ በመርዛማ ተልዕኮህ ቀባባህዉ እንጅ መፍተሄዉስ እዚህ ታላቅ አንድነት ዉስጥ ነበር ያለዉ፡፡

ሁሉም ተቃዋሚ ተሰባብስቦ (የብሄር ፖለቲካ ፓርቲ ወይም የአንድነት ፖለቲካ ፓርቲ የሚለዉ ክፍፍል ቀርቶ) አንዲት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን አሁኑኑ በስምምነት በሀሳብ ደረጃ በመንደፍ ሁሉንም ጉዳዮች ባይሆን እንኳን ወሳኝ የሚባሉት መነጋገር እና ሀገሪቱ በአንድነት የምትቀጥልበትን ብሎም ዲሞክራሲ እና የህግ የበላይነት የሚሰፍንበትን ሁኔታ ማስመር የሚቻለዉ አሁን በተቃዉሞ ደረጃ በሚገኘዉ የተለያዬ ሀይል መካከል ነበር፡፡ አሁንም ህልምህ እና ግብህ የኢትዮጵያን ህዝብ ሆነ አንተ ኦሮሞ አንደኛ የምትለዉን ህዝብ ለማዳን ከሆነ ህሳቤህ በአማራ የተደራጁትንም፡ በኢትዮጵያዊነት የተደራጁትንም ፡ በኦሮሞነት የተደራጁትንም ሳትከፋፍል የጋራ ሀገራዊ መድረክ እንዲኖር ስራ፡፡እከሌ በእከሌ ተበደለ የሚለዉን መርዝህ ግን ከአፍህ ላይ ነቅለህ ጣለዉ፡፡እስኪ አንተ ቅን ሆነህ ሁሉንም ወገን የሚያቅፍ መድረክ እንዲኖር ስራ እና የኢትዮጵያ ህዝብ ካንተ ጋር አይቁም?

ከእዉነት ከሰራህ እና ሁሉንም ሀይል ለማስተባበር ብሎም ቢያንስ አንድ የሀገራዊ የኢትዮጵያ የህልዉና የጋራ መግባቢያ መድረክ እንዲኖር ከተጋህ የኢትዮጵያ ህዝብ አንተን በመሪነት ለመምረጥ ችግር የለበትም፡፡አንተ ልብ ዉስጥ እንደሚቀጣጠለዉ የአናሳነት፡ የጥላቻ እና የማንነት ቀዉስ ችግር አይነት ችግር ኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ዉስጥ የለም፡፡የኢትዮጵያ ህዝብ በጋራ እና በአንድነት የኢትዮጵያን ህልዉና አስጠብቆ ሊመራዉ የተነሳን ማንኛዉንም ሰዉ በሰዉነቱ ሊቀበል የሚችል ታላቅ ህዝብ ነዉ፡፡ያንተ ግብህ ግን ይሄ አይደለም እና ተቃዋሚዎችን በመከፋፈል እና በማናቆር ላይ

አተኩረሃል፡፡ብልጥ ሆነህ የአማራን ህዝብ ለጀዋር መሃመድ የመጨረሻ ግብ ማስፈጸሚያነት ልታዉለዉ ደፋ ቀና ላይ ነህ፡፡

አንተ ህልምህ ሌላ ነዉ እና ይሄ ጉዳይ ያስቅሃል፡፡የኢትዮጵያ አንድነት ነገርም ይመርሃል፡፡ እኛም ያንተን ተንኮል እናቃለን እና ባንተ ከንቱ ልፍለፋ እንስቃለን፡፡ እንዲህ ሆኖም ሳለ አንተ አንጠልጥልጥለሃት የመጣሃትን የዲሞክራሲያዊ ብሄረተኝነት ጉዳይ ላይ ለምን እንደተንጠለጠልክ እና የመጨረሻ ግብህም ምን እንደሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲረዳዉ መጻፍ ተገቢ ሆኖብን እንጅ ካንተ አይነቱስ ልበ ጥቁር ሰዉ ጋር ሀሳብ መመላለስ አይገባም ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ከየተኛዉም አማራጮች የተሻለዉ አማራጭ መንገዱ አንድ ነዉ፡፡እሱዉም ዲሞክራሲያዊት አንዷት ኢትዮጵያን መገንባት ነዉ፡፡ይሄዉም በሀገሪቱ ሊመሰረት ስለሚገባዉ ህገመንግስት፡ ዲሞክራሲ፡ የህግ የበላይነት፡ የመንግስት አወቃቀር ፡ የቋንቋ ጉዳይ ፡ የወታደራዊ እና ጸጥታ ጉዳዮች ሁሉ በጋራ በመምከር ፡ በልበ ሰፊነት በመጨቃጨቅ ሁሉንም ወገን በሚያግባባ መልኩ ተቃዋሚ ሁሉ በአንኳር ጉዳዮች ላይ መግባባት ባይችል እንኳን በኢትዮጵያ የአንድነት እና የህልዉና ተጠይቅ ላይ አንድ ወጥ አቋም መያዝ ተገቢ ነዉ፡፡ኢትዮጵያ አንድ ናት በሚለዉ ጭብጥ ላይም ግልጽ ህሳቤ ላይ መደረስ ነበረበት፡፡

ከዚያም ብኋላ ኢትዮጵያን እንዴት ዲሞክራሲያዊት ሀገር እና የህግ የበላይነት የሰፈነባት ሀገር ማድረግ እንደሚገባ በስፋት መወያዬት (ማንንም ሳያገሉ) ብሎም በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መሰረት ላይ መቆም ይገባ ነበር፡፡ከዚህ ብኋላ ነበር ለስልጣን የሚደረግ ዉድድር መከተል ያለበት፡፡ይሄ ሁሉ እንግዲህ እዚህ አሜሪካ በመሸግከዉ በአንተ እና በበርካታ ኢትዮጵያዉያን ጥረት መደረግ ሲኖርበት አንተ እንደ ቁም ነገር አማራ ብሄረተኝነት ይለምልም፡ ኢትዮጵያዊነት ይኮስምን ብለህ ትለፈልፋለህ፡፡እንደ ታላቅ ኢትዮጵያን ማጥፊያ መሳሪያም በመቁጠር የአማራ ብሄረተኝነት በኢትዮጵያ አንድነት ሀይሎች እየተጠቃ ነዉ ስትል መርዛማ ሀዘንህ ታዘንበዋለህ፡፡የረሳህዉ ግን አንተን እና መሰሎችህን ቅርጥፍጥፍ አድርጎ የሚበላችሁ ከኢትዮጵያዊነት ህሳቤ በላይ የአማራ ተቃዋሚ የማያዳግም ጉልበት ያገኘ እለት እና የሀገሪቱ ወሳኝ የፖለቲካ ሀይል ሆኖ የወጣ ጊዜ ነዉ ፡፡ችግሩ ግን ያዉ የብሄር ፉክክር አዙሪት እና የብሄር የእርስ በርስ ፍጭቱ ቀጣይ ሆኖ የማያባራ አዙሪት መከሰቱ ነዉ፡፡ የማይገባህ ሆነህ እንጅ (ወይም እንዳይገባህ ሆነህ የተሰራህ አለዚያም እራስህን እንደዚያ አድርገህ የሰራህ) አሁን የምትንፈላሰስበት አሜሪካ ላንተ አይነቱ ገልቱ ሳይቀር መንቀባረሪያ ሀገር እንዲሆን ሆኖ የተሰራዉ በአንዲት ዲሞክራሲያዊት የህግ የበላይነት የሰፈነባት ታላቋ አሜሪካ የሚል ወርቃማ ህሳቤ ላይ ቆመዉ የቀደሙት ሀገር መስራች አባቶች መሰረቱን ስለጣሉት ነዉ፡፡ቢያንስ እስኪ ይሄን ሞዴል እንዴት ወደ ኢትዮጵያ ኩነት ማሸጋገር እንደሚቻል ለደቂቃ ቆመህ አስብ፡፡

===

የጀዋር መሀመድ ስብከት ለመስማት

http://www.zehabesha.com/amhar ic/archives/69693